11 ኛ ዓመት ቁጥር 5

ባህርዳር ጥር 13 ቀን 1998 ዓ.ም
Bahir Dar 20,2006

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

# ዝክረ ሕግ

# ZIKRE HIG

## Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በ
መን

**Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State**

✉ 312
ያንዱ ዋጋ ብር 3.15
Unit price

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር **123/1998 ዓ.ም**

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የኢንቨስት መንት ማስፋፊያ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ

## አዋጅ ቁጥር 123/1998 ዓ.ም

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የኢንቨስት
መንት ማስፋፊያ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ የወጣ አዋጅ

በክልሉ ውስጥ ባለሃብቶች በግልም ሆነ በጋራ ተደራጅተው በዋዕለ-ንዋያቸውን በማፍሰስ በትር ፋማ እንስቅስቃሴዎች ላይ ተማርተው የክልሉን ኢኮኖሚ ያዊ ልማት የሚያፋጥኑበትን ምቹ ሁኔታ መፍጥ በማስፈለጉ፤

ለእነዚህ ልማታዊ ባለሃብቶች የተሳለጠ አገልግሎ ት ለመስጠት ይችል ዘንድ አንድ ራሱን የቻለ

አስፈፃሚ አካላት በሕግ መመሥረትና ስልጣንና ተግባሩን በግልጽ መደንገግ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት በተሸሻለው የክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/1/ ድንጋጌ ሥር በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል።

ክፍል አንድ
ጠቅላላ

**1.** አጭር ርዕስ

ይን አዋጅ "የኢንቨስ መንት ማስፋፊያ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 123/1998 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**2.** ስመቋቋምና ተጠሪነት

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የኢንቨስት መንት ማስፋፊያ ኤጀንሲ ከዚህ በኋላ" ኤጅንሲው" እየተባለ የሚጠራው ራሱን የቻለና ሕጋዊ ሰውነት ያለው የክልሉ መንግስት አስፈፃሚ መ/ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።
2. የኤጀንሲው ተጠሪነቱ ለክልሉ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ይሆናል።

**3.** ዋና መሥሪያ ቤት

የኤጀንሲው ዋና መ/ቤት በባህር ዳር



ከተማ ሆነ እንደአስፈላጊነቱ በተመፈጡ በክልሉም ሆነ ከክልሉ ወጭ በተለያዩ አካባቢዎች ቅርንጫፍ ወይም ማስተባበሪያ ጽ/ቤቶች ይኖሩታል።

**4.** አላማ

የኤጀንሲወ ዋና አላማ በክልሉ ውስጥ በግልና በጋራየሚከሄዱየኢንቨስትመንትእንስቅስቃሴዎችን በማበረታታትና በመንደፍ ለክልሉ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት የሚኖራቸውን አስተዋጾኦ ማጐልበት ነው፡፡

ክፍል ሁለት

ስለኤጀንሲው ተግባርና አደረጃጀት

**5.**የኤጀንሲው ስልጣንና ተግባር

የኤጀንሲው በዚህ አዋጅ መሠረት የሚተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ስለኢንቨስትመንት የወጡ ፖሊሲዎችና ህጐች በክልሉ ውስጥ በትክክል መፈፀማቸውን ያረጋግጣል፣ይቆጣጠራል፤
2. የሚርቡለትን የኢንቨስትመንት ማመልከቻዎች መርምሮ አግባብ ባላቸው የኢንቨስትመንት አዋጆችና ደንቦች ላይ



የተደነገጉትን ተፈላጊ ሁኔታዎችአሟልተው ሲገኙ የኢንቨስትመንት ፈቃድ የሰጣል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ ከዚሁ የሚመነጨውን የአገልግሎት ክፍያም ይሰበስባል፤

3. የኢንቨስትመንት ህጐች የሰፈሩ ወይም የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ጐጅ የሆ ጥፋቶች ተፈጽመው ሲገኙ እንዳስፈላጊነቱ

የተሰጠውን ፈቃድ ይሰርዛል፣ ጥፋቱን
የፈፀሙት ሰዎች በሕግ እንዲጠየቁ
ያደርጋል፣

4. የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሰጣቸው ባለሃብቶች የሚያቀርቧቸው የማበረታቻ ጥያቄዎች የሕጉን ድንጋጌዎች አሟልተው ያቀረቡ መሆናቸውን አረጋግጦ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጣል፤

5. በክልሉ ውስጥ የሚገኘውን የሃብት ክምችትና የኢንቨስትመንት እድል መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፣ መረጃዎችን ለባለሃብቶች የሰራጫ ተጨባጭ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክትቶችን ለነዚሁ ያስተዋውቃል፤

6. ለባለሃብቶች ጉዳዩ በሚለከታቸው ሌሎች የክልል መስተዳደሩ አካላት መካካል የኢንቨስትመንት



ተግባራትን ያስተባብራል፣ ይቅጣጠራል፤

7. በክልሉ ውስጥ የሚካሄደውን የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ አስመልክቶ ተገቢውን የምክየመረጃ አገልግሎት ይሰጣል፤

8. ስለክሉ የሃብት ክምችትና የኢንቨስትመንት አማራጭ እድል የተጠናቀሩ መረጃዎችን እንዲሁም ስለክልሉ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ የተዘጋጁ ሪፖርቶችን ሰክልሉና አግባብ ላላቸው የፌዴራሉ መንግስት አካላት ያስተላልፋል፤

9. የሚመለከተው አካል ጋር በመተባበር

በፌዴራሉ መንግስት የኢንቨስትመንት ኤጀንሲ በኩል ፈቃድ አግኝተው በክልሉ ኤጀንሴሲ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ የሃገር ውስጥም ሆነ የውጭባለሃብቶች የሥራተግባራት ይከታተላል፣ ባለሃብቶች እዲቋቋም ይደረግ፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

10.በህግ መሠረት ውሎችን ይዋዋላል፣ ስመምምነቶችን ያደርጋል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሣል፣ ባለቤት ይሁናል።

**6.**ድርጅታዊ አቋም

ኤጀንሲው የሥራ አመራር ቦርድ፣ አስኪያጅ፣ ምክትል ስራ አስኪያጅና ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች ይኖሩታል።



ተግባራትን ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፤

7.በክልሉ ውስጥ የሚካሄደውን የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ አስመልክቶ ተገቢውን የምክየመረጃ አገልግሎት ይሰጣል፤

8.ስለክሉ የሃብት ክምችትና የኢንቨስትመንት አማራጭ እድል የተጠናቀሩ መረጃዎችን እንዲሁም ስለክልሉ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ የተዘጋጁ ሪፖርቶችን ስክልሉና አግባብ ላላቸው የፌዴራሉ መንግስት አካላት ያስተላልፋል፤

9. የሚመለከተው አካል ጋር በመተባበር

በፌዴራሉ መንግስት የኢንቨስትመንት ኤጀንሲ በኩል ፈቃድ አግኝተው በክልሉ ኤጀንሴሲ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ የሃገር ውስጥም ሆነ የውጭባለሃብቶች የሥራተግባራት ይከታተላል፣

ባለሃብቶች እዲቋቋም ይደረግ፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

10.በህግ መሠረት ውሎችን ይዋዋላል፣ ስመምምነቶችን ያደርጋል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሣል፣ ባለቤት ይሁናል።

**6.** ድርጅታዊ አቋም

ኤጀንሲው የሥራ አመራር ቦርድ፣ አስኪያጅ፣ ምክትል ስራ አስኪያጅና ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች ይኖሩታል።

**7.** ስለኢንቨስትመንት የሥራ አመራር ቦርድ

**1.** በክልሉ ውስጥ የኢንቨስትመንት ሥራዎችን በበላይነት የሚመራና የዘርፉ እንቅስቃሴዎች ተቀናጅተው የሚፈፀሙበትን ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ኤጀንሲውን የሚያግዝ የሥራ አመራር ቦርድ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

2.የቦርዱ ሰብሳቢ፣ የአባላት ጥንቅርና ዝርዝር የስራ ድርሻ በኤጀንሲው ተጠንቶ በክልሉ ርዕሰ መስተዳደር በሚወጣ መመሪያ የሚደነገግ ይሆናል።

8. ስለሥራ አስኪያጅ አሿሿምና ተጠሪነት

1. የኤጀንሲው ሥራ አስኪያጅ በርዕስ መስተዳደሩ ይሾማል።

2. የስራ አስኪያጁ ተጠሪነት ለንግድና እንዱስትሪ ቢሮ ለሿሚው አካል ይሁናል።

**9.** ስል ሥራ አስኪያጁ ስልጣንና ተግባር

የኤጀንሲው ሥራ አስኪያጅ ከዚህ በታች የተመለከቱት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 ድንጋጌዎች ሥር የኤጀንሲው የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤



2. የኤጀንሲውን በበላይነት ይመራል፣ ሥራውን ያስባብራል፣ ይቆጣጠራል፤
3. የኤጀንሲውን ሠራተኞች በክልሉ ሰቪል ሰርቪስ ሕግ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሳድጋል፣ ያሰናብታል፤
4. የኤጀንሲውን የሥራ እቅድና የማስረፀሚያ በጀት ረቂቅ ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤
5. የኤጀንሲውን በተፈቀደው የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤
6. ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች የኤጀንሲውን ይወክላል፤
7. ለሥራው ባስፈለገው መጠን ከስልጣንና ተግባራቱ ከፊሉን የኤጀንሲውን የበታች የሥራ ኃላፊዎችን በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

**10.** ስለምክትል ሥራ አስኪያጁ

1. ምክትል ሥራ አስኪያጁ በኤጀንሲውን አቅራቢነት በርዕሰ መስተዳደሩ የሚሾም ሆኖ ተጠሪነቱ ለሥራ አስኪያጁ ነው፣

2. ምክትል ሥራ አስኪያጁ በስራ አስኪያጁ ተለይተው የሚሰቱትን ተግባራት የሚያከናውን ሲሆን ሥራ አስኪያጁ በሚኖሩበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይቻልበት ጊዜና ኔታ ደግሞ እርሱን ተክቶ ይሠራል።

ክፍል ሶስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**11.** ስለበጀት

የኤጀንሲውን በጀት በክልሉ ምንግስት ይመድባል።

12.ስለሂሳብ አያያዝና መዛግብት

1. የኤጀንሲው ትክክለኛ የሆኑና የተሟሉ የሂሳብ መዛግብትን ይይዛል።
2. የኤጀንሲው የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብም ሆነ ንብረት ነክ ሰነዶች በክልሉ ዋና ኦዲተር መ/ቤት ወይም እርሱ በሚወከለው አካል በየጊዜው ይመረራሉ።

13. ተፈፃሚነት ስለሚኖራቸው ህጐች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ህግ፣ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሰራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዩች ላይ ተፈፃሚነት ኤይኖረውም።



14. መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ

በአዋጅ ቁጥር 4/1988 ዓ.ም / እንደተሸሻለ/ ተቋሞ የነበረው የኢንቨስትመንት ጽ/ቤት መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት ወደ ተቋቋመው የኢንቨስትመንት ማስፋፊያ ኤጅንሲ ተላልፈዋል።

**15.** መመሪያ የማውጣት ስልጣን

በዚህ አዋጅ  አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2 ስር የሰፈረው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል፡፡

16. አዋጅ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግስት ዝክረ-ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ባህር ዳር
የካቲት **13** ቀን **1998** ዓ.ም

አያሌው ጐበዜ
የአማራ ብሔራዊ ክልል
ፕሬዚዳንት